# "ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል"

አባቶቻችንና እናቶቻችን የጽድቅንና የኩነኔን መኖራቸውን ስለማይጠራጠሩ ለትንሹም ለትልቁም መለኪያቸው ጽድቅና ኩነኔ ነበር:: በስንዴ መካከል እንክርዳድ እንዳለ በጤናማ ሕዝብ መካከልም ጥቂት የሰው እንክርዳድ መኖር ግድ ነውና፥ የጽድቅንና የኩነኔን መኖርና አለመኖር የሚጠራጠሩ ጥቂት እንክርዳዶች መከሰታቸው አልቀረም:: *"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖሩም ባይኖሩም፥ ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም"* ብለው የጽድቅንና የኩነኔን መኖር የሚአጠራጥር ዘይቤ ፈጠሩ:: ደግነት ከክፋት መሻሉን ግን በፍጹም አልተጠራጠሩም ነበር::

ወደ ጽቅድ የሚአመራው ክፋት እንዳልሆነ ከክፋትም ደግነት እንደሚሻል ሴቱም ወንዱም ሲመሰክረው ለዘመናት ኖሯል:: በዚህ ጽድቅ መስመር ሳይወላውሉ ቀጥ ብለው በመቆም እንደበታቸውና ተግባራቸው ሳይጋጭ ሩጫቸውን የፈጸሙ ታላላቅ ሰወች ብጹአን ቅዱሳን ነበሩን:: ፍጡራን ናቸውና በሥጋ የሉም:: አልፈዋል:: የተናገሩት ቃላቸው ግን ከነሱ ጋር የሚአልፍ አይደለም:: ዛሬም ሕያው ነው:: *"አንድ ቃል የነገረህን እንደአባትህ፥ ሁለት ቃል የነገረህን እንደፈጣሪህ አክብረው"* እየተባልን ስላደግን እንደነሱ ወደ መቃብራችን እስክንገባ የጽድቅ ቃላቸውን ለአብነት  እንጠቅሳለን::

*"ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል"* የሚለውን ቃል በገሐድ ያወጀው የመምሕራንና ያባቶች ፈጣሪ ነው ብለን የምንከተለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ከክርስትና እምነት ውጭ ያሉትም ቢሆኑ ነቢይ ነው: ከተራ ሰው ሁሉ በላይ ነው ብለው ስለሚአምኑት፥ እንደ ክርስቲያኖች ለቃሉ ባይሞቱለትም: ቃሉን አክብረው መቀበል ይገባቸዋል:: እኛ ክርስቲያኖች ግን የነብያትም የሁላችንም ፈጣሪ ነው ብለን ስለምናምነው የተናገረውን መቀበል ብቻ አይደለም ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናል:: ጽድቅን ለመፈጸም ያማያስችሉ ሕይወትን የሚጠይቁ ኃይሎች እንኳን ቢገጥሙን ለሥጋችን በመሳሳት ወደኋላ ማለት አይገባንም:: ምክንያቱም *"ይገባናል"* የሚለው ቃል አማራጭ የሌለው የታወጀ ትእዛዝ ነው:: ይህ የጽድቅ አዋጅ አጋጣሚ (coincidence) የፈጠረው አይደለም:: ክርስቶስ እራሱን በሥጋ ከመግለጹ በፊት በብዙ ምሳሌወችና ትንቢቶች ለሰው ልጅ መታቀዱን ሊቃውንት አባቶቻችን በግእዝ ቋንቋቸው ገልጸው አስተምረውናል::

በነገራችን ላይ ይህን ጦማር (ጽሑፍ) ለመጻፍ መንፈሴን ያነሳሳው ስለጥምቀቱ መሠረታዊው ትርጉም ለመግለጽ አልነበረም:: *"በጥምቀቱ በአል አከባበር ለምን እኛ ከሌሎች ኦርቶዶክሶች ተለየን?" እራስሕስ እንዴት ታየዋለህ?* የሚል ጥያቄ ከብዙ ሰወች ቀርቦልኝ ሳስብ፥ የጥምቀት በአል ዋና አላማ የጽድቅን አዋጅ መግለጽ እንደሆነ አባቶች ደጋግመው የነገሩኝ ትዝ አለኝና: *መሠረታዊ ትርጉሙን* አሁን ካለነው የቤተ ክርስቲያን ሰወች ጋር እያነጻጸርኩ መቃኘት ጀመርኩ:: ቤተ ክርስቲያናችን ቅድስትና የምንኮራባት መሆኗን እጅግ የበለጠ ተረዳሁ:: ስርአቱን ያቀነባበሩት የቀደሙ ሊቃውንት አባቶቻችንም እጅግ የሚአኮሩ እንደነበሩ የበለጠ ተገነዘብኩ:: ነገር ግን የበአሉ ዋና አላማና መልእክት ከኛ ከካህናቱና ከዘመኑ *መንፈሳዊያን* መሪወች ጋር እጅግ የተጋጨና ፍርቅ ሆነብኝ:: በጥምቀቱ የታወጀው የጽድቅ አዋጅ ጨርሶ መበላሸቱ ተሰማኝ:: ጥያቄው ከተነሳ ዘንድ አባቶች ሊቃውንት አበው ያስቀመጡት *መሠረታዊ* ትርጉም ቢገለጽ ጽድቅን ሁሉ ለማጥፋት የምናደርገውን ሙከራ ግልጽ አርጎ ከፊታችን እንደተዘረጋ መስታወት የሚአሳየን መሆኑን አስተዋልኩ:: ጽሑፉ በዛ ለማንባብም ጊዜ የለንም አትበሉኝና ስለጥምቀቱ በአል ሊቃውንት አባቶች የነገሩንን አበይት የሆኑትን *መሠረታውያን* ማብራሪያወች ከጠቅላላ ትርጉሙ ትንሽ ቁንጣሪ ወስደን (autopsy) ብንመረምረው: ስለበአሉ *መረዳት* ብቻ አይደለም፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ *መሪ*ወችና በሕዝቡ መካከል ያለውን ሁኔታ በግልጽ ያሳየናል:: *መሠረተ* ትርጉሙም የሚከተለው ነው::

*"ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ"* እንዲሉ፥ የነገረ መለኮት ትርጉማችን በምሳሌና በመለኪያ የተቀረጸ ነው:: ፪ ምሳሌወችን ብቻ እጠቅሳለሁ:: ፩ኛ በመጽሐፈ (ነገሥት ካልዕ ምዕ ፪:፲፱-፳፩) እና ፪ኛ በዚሁ መጽሐፍ ምዕ ፮: ከቁጥ ፩-፯) ላይ የሰፈሩት ናቸው:: በምዕራፍ ፪ ከቁጥር ፲፱ እስከ ፳፩ ድረስ ያለው ታሪክ የሚናገረው: ኤልሳዕ በመረረው በኢያሪኮው ውሀ ውስጥ ስለከተተው ጨው ነው:: ይህ በውሀው የገባው ጨው ለሰውና ለእንስሳ ሁሉ መርዝ የነበረውን ውሐ ወደ ሕይወት ሰጭነት ለወጠው:: ጌታችን ክርስቶስም ይህን ምሳሌ አማናዊ ለማድርግ መለኮታዊ ባሕርዩን ከሰባዊ ባሕርያችን ጋራ አዋሕዶ የመረረውን ሕይወታችንን ለወጠው:: አጣፈጠው:: በነገራችን ላይ

በጥንቱ አማረኛችን *"ጨውተው ወይም አጫውተው"* ማለት አጣፍጠው ማለት እንደሆነና አጫውተኝ ማለት አስደስተኝ ማለት እንደሆነ አባቶች ይናገሩ ነበር:: *"ጨዋታ"* ማለትም ከግብዝነትና ከማስመሰልነት እንደ ሕጻን ልብ ከጠራ ልብ የሚመነጭ ኀብረት ማለት ነው::

አሁን ደግሞ ፪ኛው በ፪ኛ ነገ ፮:፩-፯) ያለውን ምሳሌ እንመልከት ታሪኩ እንዲህ ነው፥ ከነብያት ልጆች አንዱ ምሳር ተውሶ ጫካ ሄደና እንጨት ሲቆርጥ ምሳሩ ከጆታው ወልቆ ባካባቢው ካለው ውሐ ገብቶ ብረት ነውና ሰመጠበት:: አዘነ ደነገጠና ጮኹ:: በኤልሳዕ ምክር እንጨት አምጥቶ ምሳሩ በሰመጠበት አካባቢ ወደ ውሐው ጣለው:: የምሳሩ ክብደት ወደ እንጨቱ፥ የእንጨቱ መንሳፈፍ ባሕርይ ወደብረቱ ተዛወረ:: ይህ በመጥረቢያውና በቅርፍቱ መካከል የተካሄደው የባሕርይ ቅብብሎሾ ምሳሌ በመለኮትና በትስብት መካከል ክርስቶስ ሰው ሆኖ በተጸነሰባት ቅጽበት ተፈጸመ:: በጥምቀቱ አወጀው:: መስጠም የሚገባው ብረት ተንሳፈፈ:: መንሳፈፍ የሚገባው እንጨት ሰጠመ:: እንደዚሁም እኛ በኃጢአት እመቅ ሰጥመን እንዳንቀር ክርስቶስ በኛ ባሕርይ ውስጥ ሰምጦ ገብቶ በመወሐድ የኛን የኃጢአት እዳ በደል ተሸከመልን የሱን ጽድቅ ስለሰጠን ከዘላለም ጥፋት አወጣን:: ራሱን የጽድቅ መርከብ አድርጎ እኛን በመሸከም በዘላለም ጽድቅ ላይ እንድንሳፈፍ አደረገን:: ምሳሌው ይህ ነው:: ሁለቱም ምሳሌወች በተለያዩ አቀራረባቸው የሚገልጹት ክርስቶስ በኛ ሕይወት ውስጥ ገብቶ ከኛ ጋራ በመዋሐድ ከጥፋትና ከመረረ ሕይወት ማውጣቱን ነው::

የክርስትና መለኪያ ነብያት ናቸውና አሁን ደግሞ ወደ መለኪያው እንሄዳለን:: "ደዌአችንን ተቀበለ: ሕማማችንንም ተሸከመ: ስለ መተላለፋችን ቆሰለ: ስለ በደላችንም ደቀቀ: የደኀንነታችን ተግሳጽ በእርሱ ላይ አኖረ የእግዚአብሔር ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ብዙ ሰዎችንም ያጸድቃል"(ኢሳ ፶፫:፭-፲፪ የሚለው ነው:: ይህንን ያፈጻጸም ሂደት የተመለከተ ነቢዩ ኤርምያስም የክርስቶስን ስም "ጽድቃችን" ብሎ ሰይሞታል:: ይህም ማለት በሠራነው ኃጢአት ዘቅጠን ለዘላለም እንዳንጠፋ ክርስቶስ የመዳናችንና የጽድቃችን መርከብ ሆነን:: በሱ መርከብነት እንድንሳፈፍ አደረገን ነው:: (ኤር ፳፫:፮)

አስቀድሞ በትንቢትና በምሳሌ የተነገረውን ጽድቅ፥ ጊዜው ሲደርስ ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ አወጀው:: ይህ የጽድቅ አዋጅ የሶስትነታቸው ስምምነትና ፈቃድ ክነውን ስለሆነ ስላሴ በተለየ አካላቸው መሰከሩለት:: ምድራዊ አዋጅ በመድፍ እንደሚታጀብ፥ ይህ የጽድቁ አዋጅ ሲታወጅ ሰማያት በመከፈት አጀቡት:: የክርስትናን እምነት የሚከተሉ ሁሉ ክርስቲያኖች ክርስቶስ የዘረጋውን ይህን ጽድቅ የመልበስ ግዴታ እንዳለባቸው ለማሳየት *"ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም"(ማቴ ፭:፳)* ብሎ ክርስቶስ ቁርጥ ያለ አዋጅ አወጀ:

በዚህ መልክ ክርስቶስ ያወጀውን የጥምቀት በአል እኛ የምናከብረው *"ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ"* በማለት በእጃችን ያለውን ሁሉ ነገር በመጠቀም ነው:: ዮሐንስ በራእዩ ሰማይ ተከፍቶ ሲመለከት በሰማይ ባለው ቤተ መቅደስ ያለውን ሰማያዊ የቃል ኪዳኑን ታቦት አይቷል:: (ራዕይ ፲፩:፲፱) እኛም ይህን ምሳሌ ከባሕላችን ጋራ በማዛመድ በጥምቀቱ ጽድቅ ሁሉ ሲፈጸም፥ የቤተ መቅደሶቻችንን በሮች በመክፈት በየቤተ መቅደሶቻችን ያሉትን የቃል ኪዳን ጽላቶች እንገልጻቸዋለን::

ከዚህ በላይ ስለጥምቀቱ የጠቀስኳቸውን ምሳሌወችንና ትንቢቶችን እንደ ባትሪ ብርሐን በኖራ በተለሰነው መቃብር ውስጥ ወዳለው ሬሳነታችን በመርጨት ግልጥልጥ አርገን ለመረዳት ወደ ዝርዝር ሐተታ እገባለሁ:: በምሳሌና በትንቢት እንደተገለጸው ይህ ጽድቅ ክርስቶስ ሲጠመቅ ያወጀው ያመነበት ሁሉ ሊፈጽመው የሕይወት ግዴታ ነው:: ይህ የጽድቅ ቃል *"ሰማይና ምድር ቢያልፍ የተናገርኩት ቃል አያልፍም"* ብሎ የማይገሰስ መሆኑን አረጋግጦ ተናገረ:: ጻድቃን ሰማእታት ብለን የምናከብራቸው *"ተከተል አለቃሕን ተመልከት አላማህን"* እንዲሉ አለቃቸውን ክርስቶስን በመከተል፥ አላማቸውን (ጽድቅን) በመመልከት በተናገረው ቃል ጸንቶ የተሰቀለውን ክርስቶስን የተከተሉ ናቸው:: ጌታችን የላከኝ አባቴ ነው ይላልና፥ የላከው አባቱ *"የተናገርኩት ከሚጠፋ የወለድኩት ይጥፋ"* በሚለው ቃል ጸንቶ: አንድ ልጁ ስለቃሉ በሥጋ እንዲሞት ላከው:: አባቶቻችንም ይህን መሠረት በማድረግ *"የተናገሩት ከሚጣፉ የወለዱት ይጥፋ"* የሚለውን የሞራል ንግግር ይሉኝታ በምንለው ኢትዮጵያዊ ባሕላችን ውስጥ ከተቱት:: *"ኢትትሐጎሉ እምፍኖተ ጽድቅ" (መዝ ፲፪:፵፪)* ማለትም *"ከጽድቅ መንገድ ዝንፍ አትበሉ"* በሚለው የዳዊት ቃል አፋችንን እንድንፈታ አደረጉ:: በማነኛውም ሥጋችንን በሚአጓጓ ነገር ስንፈተን በውስጡ ያለውን የሚአረካ ሽታ እንደሚአመነጭ የሽቶ ቢልቃጥ ክርስቶስ በጥምቀቱ ያወጀውን ጽድቅንና እውነትን ለማፍለቅ ነበር:: ካፋችን የሚወጣው ቃል ወቅቱን

ጠብቆ ጠልና ልምላሜን እንደሚአርከፈክፍ የበረከት ዝናም እንዲሆንም ነበር::

አሁን እያደረግን ያለነው በተለይም ሞተናል መንናል መንኩሰናል ቀሰናል ተጰጵሰናል ከምንለው ሁሉ የሚፈልቁት በግብራችን የምናሳየው ሁሉ ጌታችን ክርስቶስ የፈሪሳውያንን ባሕርይ ለመግለጽ በማቴወስ ወንጌል በምዕራፍ ፳፫ ላይ የደረደራቸው በግብዝነት ላይ የተመሰረቱ ጠባዮች ናቸው:: *"በኖራ የተለሰኑ መቃብሮች"* አላቸው:: የሚሸተውን የፈረሰ እሬሳ የተሸከመ መቃብር የሚመስል አስከፊና አሰቃቂ ባሕርይ እንደሆነ የተናገረው ጌታችን ነው:: የሚአስፈራ የሚአስደነግጥ የሚዘገንን የሰው ሬሳ የተሸከመውን መቃብር ለመግለጽ የሚጠቀስበት ሰው ምንኛ እጅግ በጣም መፈጠሩን የሚአስጠላ ነው? ባስደንጋጭና ዘግናኝ ባሕርዩ ከፈጣሪውና ከፍጡር ክልል ውጭ ርቆ ሄዶ የጠፋ መሆኑን የሚገልጽ ከዚህ የከፋ ምሳሌ የሚገኝ አይመስለኝም::

የግብዝነት ባሕርይ የጎነጣቸው አንዳንድ ሰወች እንዲህ ያለ ነገር ሲከሰት *"አትንኩት እንደተከደነ ይብሰል"* ይላሉ:: ይህም አባባል *"የተከደነ የማይገለጥ የለም"* ብሎ ከተናገረው ከጽድቅ ባለቤት ከክርስቶስ ጋራ የሚጋጭ ነው:: መገለጥ አለበት:: ልብና ሕሊና በክፋትና ጭካኔ የጠቆረ መሆኑ እየታወቀ:- ለሰው ለመታየት ጥቁር ቀሚስ ማንዘርፈፍ፥ ኩፌት (ቆብ) መድፋት፥ ባለ ዘርፍ ቀጸላ መከናነብ፥ ከሩቅ የሚፈልቅ የወርቅ መስቀል እንደ አሸንክታብ በደረት ላይ ማንዠርገግ፥ በሄዱበት ቦታ ሁሉ በከበሬታ ወንበር ላይ መቀመጥ፥ በጉባዔው ሙያ ሳይበስል በድፍረት እራስን መምሕር ብሎ መሰየም፥ በረዥም ዘመን አገልግሎት ለአረጋውያን አባቶች ይሰጥ የነበረውን ቁምስና ነጥቆ በመውሰድ ቆሞስ እገሌ ብሎ እራስን መጥራት፥ በትምርህቱ በሙያው በአመክሮው ሳይቆዩ በከተማ ያደጉ ጎረምሶች ሁሉ ሊቀ ጳጳስ ነን እያሉ በድፍረት ሕዝቡን ለመባረክ መሞከር:: የጸሎት ሰው መስሎ በመታየት የየዋሆችን ልብ ለማፍዘዝ ገንዘባቸውንም ለመዝረፍ ምን ማለት እንደሆነ ራሳቸው የማያውቁትን የተወላከፈ ግእዝ ማነብነብ፥ ሳያምኑ ሌላውን ለማሳመን ውቅያኖስ አቋርጦ ባሕር ተሻግሮ መዞር፥ ሐሰት መናገር፥ በሐሰት መማል፥ ለተቀደሰው አገልግሎት የተሰበሰበውን ሙዳየ ምጿት በመዝረፍ የራስን ቪላ መገንባት፥ በቅሚያና በስስት አዚም ሰክረን ምእመናኑን በዓለማውያን ዳኞች አደባባይ ፊት እየከሰሱ መሟገት፥ በአውደ ምሕረቱና በአዳባባይ የወገን ደም ሲፈስ አለመደንገጥ፥ በጥቅሉ የሚሸተውን የፈረሰ እሬሳ የተሸከመ መቃብር የሚመስል አስከፊና አሰቃቂ ባሕርይ መሸከም፥ እነዚህ ሁሉ ወዮታ የተሸከሙ የጽድቅ ተቃራኒወች ሲመነጩ በግልጽ እየታዩ የሚአመነጩት ሰወች ብፁዕ ቅዱስ ተብለው መጠራትና መጥራት፥ ጠሪውንም ተጠሪውንም የሚሸተውን የፈረሰ እሬሳ የተሸከመ መቃብር ያደርጋል:: የተለሰነ መቃብር ከመሰሉ ጋራ *"ጽድቅ"* የታወጀበትን የጥምቀትን በአል ለማክበር አብሮ መሰለፍ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ የከበደ ነው::

ከመስከረም እስከ ጳጉሜን ድረስ ያሉት ሁሉ የአመት በአላት የመንፈሳዊ ባሕርያችን መመርመሪያ ወቅታውያን የእድሜአችን አንጓወች ናቸው:: በነዚህ ወቅታውያን የአመት አንጓወች በጽድቅ ወይም በበደል መስመር ላይ መሆናችንን የምንመረምርባቸው ምዕራፎች ናቸው:: በያመቱ የምናከብረው የጥምቀት በአል፥ ባለፈው አመት እና በሚቀጥለው አመት መካከል ላይ ቆመን: ካምናው ጥምቀት ጀምሮ እስከዘንድሮው ጥምቀት ቀን ድረስ የሰራናቸውን *"ጽድቅ ሁሉ"* የምንመረምርበት ዓቢይ በአል ነው:: በሌላ በኩል ከዘንድሮዋ ጥምቀት እስከ ከርሞዋ ጥምቀት ድረስ የምንጓዝበትን የጽድቅ አውራ ጎዳና የምንዘረጋበት ነው:: ምክንያቱም *"እንግዲህስ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል "*ብሎ ጌታችን ጽድቅን በገሐድ ያወጀበት እለት ነውና:: (ማቴ ፫:፲፭)

የጥምቀትን በአል ስናከብር ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ጽድቆች ጋራ ተያይዘው የሚፈጸሙ ባሕላውያን ትርፍራፊወች አሉ:: እነሱም ሆታወች ሽብሸባወችና የድግስ አይነቶች፥ ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እያልን የምንለብሳቸው የልብሶቻችን አይነቶች ናቸው:: ሌሎችም ሐተታወች አሉ:: ከቤት አሰራራችንና ልብሳችን ጀምሮ እስከምንጎርሳቸው ምግቦቻችን ከኛነታችን ጋራ የተወሐዱት እንደዛሬው ሕይወታችን ከጽድቅ ተለይተው እንደገፈት ካላጠለሉ በቀር ከታሪካችንና ከባሕላ ጭምር ነው:: የጥንት አባቶቻችን ተጨንቀውና ደክመው የክርስትናን እምነት ከባሕላችንና ከተሪካችን ጋር አስማምተው ሰርተውት ነበር:: የውጭ አገር ሊቃውንትም የምንከተለውን የመጽሐፍ አተረጓጎማችንን ስልት (Ethiopic -cultural theology) ብለው ሰይመውት ነበር:: ሆኖም ስንት ጊዜ ጎርሰን እንደምንጠግብ፥ ስንት ሊትር ውሐ ጠጥተን ከጥማችን እንደምንረካ ትኩረት ሰጥተን ለማወቅ እንዳልሞከርን: አባቶቻችን ደክመው የሰሩትን ለመረዳት ትኩረት ባለመስጠታችን የገጠመን የሞራል ውድቀትና የመንፈስ ባዶነት እንዴት እንደሚቃና ለማወቅ እጅግ አስጨናቂ እየሆነብን ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ባዶ ቀፎነት፥ አገራችን ኢትዮጵያ ወደ ባዶ ወናነት በመስጠም ላይ ናቸው::

ማንም ሰው እስከሞቱ ድረስ ሊቆምለት ሊቆረቆርለት የሚችለው ለተረዳው ነገር ነው:: እላይ እንዳልኩት ስለጥምቀት በአል በይፋ የታወቀው *"ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ"* የሚለው እና ሆታወች ሽብሸባወችና የድግስ አይነቶች ናቸው:: የበአሉ ዋና ምሥጢር በነዚህ ተሸፍኗል:: ከበአሉ ዘርፎች አንዱ ይቅር ቢባል መቅረት የለበትም ብለን ባሕሉን ለመጠበቅ ሁላችንም ያለንን ኃይል መጠቀማችን አይጠረጠርም:: ልንሞትለት የሚገባን የጥምቀት በአል ዋናው አላማ *"ጽድቅ"* ሲናድ ያለንን ሁሉ ኃይል አስተባብረን የሚንደውን ኃይል መናድ አልቻልንም:: እንዲአውም የነበረንን ጽድቅ የገፈፈውን ኃይል ያፈረሰው ጽድቃችን እርስ በርሳችን የሚአጋጭበት መሳሪያ ሆኖታል:: እየሰየመ ወደ ሕዝብ ለሚልካቸውም ምንደኞች እንድነታችንን እየሰበሩ ለመበታተን መልካም አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል::

ሁላችንም ለሰከንድ ቆም ብለን በማሰብ፥ ይህ አመታዊ የጽድቅ አዋጅ የተፈጸመበት የጥምቀት በአል ከሌሎች ክርስቲያኖች እኛን ልዩ ያደረገበትን ሁኔታ እንመልከት:: ይህም ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ የተጠየኩት ጥያቄ ነው:: ልዩ ያደረገን ከመጽሐፍ ቅዱሱ የወጣና ያፈነገጠ ለክርስትና ትምህርት እንግዳ በመሆኑ አይደለም:: ሌሎች ክርስቲያኖች ካሜራቸውን ተሸክመው በያመቱ ወደኛ የሚጎርፉት እራሳቸው በአገራቸው ለማክበር ሜዳ፥ ካህናት ስለሌሏቸውም አይደለም:: ከኛ አገር ሜዳ እጅግ ሰፊ የሰማይ ስባሪ የመሰለ ሜዳ አላቸው:: እጅግ የረቀቁ ሊቃውንት ካህናትም አሏቸው:: እነሱ እንደኛ የማያከብሩት ክርስትና በየአገራቸው ሲገባ የተቀበሉት የመጀመሪያ ክርስቲያን አባቶቻቸው cultural theolojy ስላላደረጉላቸው ብቻ ነው:: ይህ የጥምቀት በአል አከባበር እንደ ዶክትሪኑና እንደቀኖናው ከኦሬንታሎች ጋራ የማንጋራው፥ የግላችን ኢትዮጵያዊ በአል ነው:: የግላችን ነው ስል ካብነቱ አተረጓጎማችን ክልል ወጥቶ፥ ከአኀት አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት አፈንግጦ: ከካቶሊኮች ተቀላውጦ በኛ ዘመን እንደታወጀው እንደነገረ ማርያሙ ነው ማለቴ አይደለም:: ባለመሆኑም ነቃፊወቻችን መንቀፍ ያልቻሉት ይልቁንም ወሸው ያሰደነቃቸው ጉዳይ ነው:: የዓለምንም ቀልብ የሳበ ነው:: የክርስቶስን ጽድቅ ለለበሱና ለመልበስም ለሚናፍቁ ሁሉ ይህ ሥርአታችን ስሜት የሚአረካ ነው:: ከአገራቸው ውቅያኖስ እያቋረጡ ወደኛ የሚመጡት ጎብኝወች ከጽድቅ ባዶ የሆነውን የሆታና የሽብሸባ ድራማ ለማየት አልነበረም:: በጥምቀቱ ክርስቶስ ያወጀውን ጽድቅ ለራሳችን ሕዝብና ላገራችን በተግባር ስንፈጽመው ለማየትና ከኛ ለመማር ነበር::

በየአመቱ ስናከብረው ካለፈው (ካምናው) በአላችን እለት ጀምሮ እስከዘንድሮው እለት ከተፈጸሙት ሁሉ የ"*ጽድቅ*' ተቃራኒወች ለመሸሽና ለመራቅ ጽድቅን (እውነትን) ለመመስከር ስንታገል ይህ አመት አለፈ ብለን ከተለያዩ አቅጣጫወች ወደኛ በሚጎርፉት ሰወች ፊት ቆመን ለመመስከር ነበር:: ዘንድሮ ደግሞ ከዚህች እለት እስከ ከርሞዋ እለተ-ጥምቀት ድረስ እግዚአብሔር ቢአቆየን *"ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም"* መዘጋጀታችንን ለዓለሙ ሁሉ ባደባባይ ለመግለጽ ነበር:: አልተቻለም:: የሚአሳዝነው በያመቱ የምናከብረው የጥምቀቱ በአል ክርስቶስ ጽድቁን ከማወጁ በፊት የነበሩት ፈሪሳውያን ከፈጸሙት ኃጢአትና በደል የኛ እጅግ የከፋና የባሰ እንደሆነ የሚጋለጥበት ቀን መሆኑ ነው:: ፈሪሳውያን ተቃራኒውን ሁሉ የሚፈጽሙ ጽድቅ የጎደላቸው ስለነበሩ የጥምቀትን በአል ማክበር ቀርቶ አሳቡም አልነበራቸውም:: ክርስቶስ ከነገራቸውም በኋላ ሊአከብሩት ይቅርና ጽድቅን ለማዳፈን የጽድቅን ሁሉ ባለቤት የሆነውን ጽድቅን ያወጀውን እራሱን ክርስቶስን አንድ ጊዜ ገደሉት::

እኔን ያስጨነቀኝ ከውጭ ለመጣው ታዛቢ በክርስቶስ መስመር ቆመን መታየት አለመቻላችን ብቻ አይደለም:: ከፈሪሳውያን መስመር እጅግ ርቀን ክርስቶስን ደጋግመን በመስቀላችን ኢትዮጵያን ሌላይቱ ቀራንዮ ማድረጋችን ነው:: ፈሪሳውያን የጽድቅ ተቃራኒ በመሆናቸው የተባለውን ሁሉ የኃጢአት አይነት ቢፈጽሙም፥ የጽድቅ መዝገብ የሆነውን የቃል ኪዳኑን ታቦት በራሳቸው ተሸክመው፥ ቀሚሳቸውን አንዘርፍፈው የክርስቶስን መስቀል በደረታቸው አንዠርግገው ጻድቅ ቅዱስ ብጹዕ የሚአስመስለውን መሳሪያ ሁሉ በመጠቀም እኛ እያደረግን ያለውን ሁሉ የጽድቅ ተቃራኒ አላደረጉም:: የሕዝባቸውን መከራ በመሸከም ስለሕዝቡ እንደ ክርስቶስ ሰምጠው ባያድኑትም፥ ሕዝቡን አላሰመጡትም:: እኛ ግን ሸሽተው የተደበቁትን ሁሉ ወጣቶች እየፈለግን ሊውጣቸው ለሚፈልገው ዘንዶ በማጉረስ ሕዝቡን በዘንዶው ሆድ ውስጥ እያሰመጥነው ነው::

አሁንም እላለሁ፥ እኛን የሚአስወቅሰን ጽድቅን አለመፈጸማችን ብቻ አይደለም:: *"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም"* የሚለውን ገልብጠን "ከደግነት ክፋት ሳይሻል አይቀርም" እያልን ክፋትን በግብራችን መስበካችን ነው:: ቀድሞ *"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም*

ባይኖርም ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም" የሚለውን የሚተርቡ ጥቂት ነበሩ፡፡ ዛሬ ግን እኛ የዘመኑ ካህናት፥ በተለይም ዓለምን ንቀን ለዓለም ምኞት ሁሉ ሞተናል የሚሉት ጳጳስ ከደግነት ክፋትን በመምረጥ ጽድቅና ኩነኔ የለም ወደሚለው ክህደት ሕዝቡን እየመሩት ነው፡፡ በጭካኔና በጥላቻ አስጨንቀንና አፍነን የያዝነው ሕዝብ፥ ሕይወት እንዲመረው፥ የተወለደባትን አገር አምርሮ እንዲጠላት፥ የሚወደውንና አክብሮ የያዘውን እምነት፡ ባሕልና ታሪክ እንዲጠራጠር እያደረግነው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕይወት ይኖር ዘንድ በሱ ፋንታ የኛ ሕይወት ይስጠም እያሉ ያለፉት እነ አቡነ ጴጥሮስ እነ መምሕር ገብረ ኢየሱስ ቀና ብለው የዘመኑ ጳጳሳት የሚአደርጉትን ቢአዩ የሚናገሩትን ቢሰሙ
ምን ይሰማቸው ይሆን?

ክርስቶስ በጥምቀቱ ያወጀውን "ጽድቅ ሁሉ" ከሰውነታችን ከባሕላችን ከታሪካችን አውጥተን ጣልነው፡፡ ደመሰስነው፡፡ ሕይወታችንን ባሕላችንን ታሪካችንን የሚሸተውን የፈረሰውን አስከፊውንና አሰቃቂውን የአስፈሪውን የበሰበሰውን የሚአስደነግጠውን የሚዘገንነውን ሬሳ የተሸከመ መቃብር አደረግነው፡፡ ሽተታችሁን ከረፋችሁን ዘገነናችሁን እያለ በሚጮሕብን ሕዝብ ፊት ዘወር ማለት ባለመቻላችን ከሕይወት የራቀ ነፍስ የተለየው ደርቆ የከረረ እሬሳ መሆናችንን ደቂቀ አዳም አረጋገጠው፡፡

ለብሔራዊ እርቅ የነቃን የበቃን ነን ብለው በሕዝብ ፊት ከቆሙ በኋላ "ጽድቅን ሁሉ" የሚደመስሱ አንዳንድ ሽማግሌወች በተከሰቱባት፥ መነኩሴው ጳጳሱ ኃጢአትና በደል በይፋና በአዋጅ በሚያካሄዱባት በዛሬይቱ ምድራችን፥ እኔ እዳ በደል የሌለብኝ ንጹሕ እንደሆንኩ እናንተም ንጹሀን ሁኑ ብሎ፥ ለግፈኞቹና በደለኞቹ ምእዳን መስጠት የሚችል ማነው? ሕይወት በመረረው በመከራና በስቃይ እመቀ-እመቃት ውስጥ በመስጠም ላይ ባለው ሕዝብ መካከል ቆሞ፥ ፊቱን ወደ ግፎኞቹ አዙሮ፥ እያፈሰሳችሁ በምታጎርፉት ኢትዮጵያውያን ደም የምትዋኙ እናንተ ርጉማን! እኔ ከዚህ ደም ንጹሕ እንደሆንኩ አናንተም ንጹሐን ሁኑ! ጽድቅን ሁሉ አርክሳችኋልና ተጸጸቱ! የበደላችሁትን ሕዝብ ድንጋይ ተሸክማችሁ እግሩ ላይ በመውደቅ ይቅርታ ጠይቁ! ብሎ በኢትዮጵያውያን ደም ወደተነከሩት ግፈኞች ውሐውን የሚረጨው የትኛው ቅዱስና ብፁዕ ነው?

የጽድቅ ባለቤት ክርስቶስ የዛሬ አመት ያገናኘን!